በ2018 ዓ/ም ለ1ኛ ጊዜ

የወጣ መደበኛ የመሬት ሊዝ ጨረታ ማስታወቂያ

በቤንች ሸኮ ዞን በሚዛን አማን ከተማ አስተዳደር የሚዛን አማን ከተማ ማዘጋጃ ቤት በሚዛን-አማን ከተማ አስተዳደር ቀበሌ ከተማ ቦርሳ መንደር እና በሚዛን 2ኛ ደረጃ ት/ቤት አካባቢ ለድርጅት አገልግሎት የሚውሉ ቦታዎችን በሊዝ ጨረታ አወዳድሮ ማስተላለፍ ይፈልጋል፡፡

ስለዚህ ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ የማይመለስ ብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ በመክፈል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በሥራ ቀናት ከማዘጋጃ ቤቱ የመሬት ልማትና ማናጅመንት የሥራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 03 መውሰድ ይችላል ፡፡ በተጨማሪም በሚዛን አማ. ኤም ሬዲዮ እንዲሁም በመ/ቤቱ ዌብሳይት www.mizanamanmuc.gov.et የምንገልፅ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ማንኛውም ተጫራቾች ህጋዊ የሆነ ማንነታቸውን የሚገልፅ መታወቂያ በመያዝ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 (አሥር) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለቦታዎች የሚያቀርቡትን ዋጋ የሚከፍሉትን የሊዝ ቅድሚያ ክፍያ እና ከፍሎ ማጠናቀቅያ ጊዜ በጨረታ ማወዳደሪያ ዋጋ መመሪያ ሠነድ ላይ በመመላት እና ኢንቨስተር ፖስታውን በማሸግ በተዘጋጀው የጨረታ ሣጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

1. አንድ ተጫራች ከአንድ ቦታ በላይ በአንድ ጊዜ መጫራት አይችልም፡፡ ከቀረቡት የጨረታ ቦታዎች መካከል በአንዱ ቦታ ላይ ብቻ መርጦ መጫራት አለበት ፣
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለሚወዳደሩበት ቦታ የጠቅላላ የቦታው ስፋት በመነሻ ዋጋው ተባዝቶ ከሚገኘው ውጤት 5 በመቶ በባንክ በተረጋገጠ የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ (CPO) ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
3. የጨረታ ሠነድ ሽያጭ 10/09/2018 ዓ.ም መሸጥ የሚጀምር ሲሆን የሚጠናቀቀው 24/09/2018ዓ.ም በ9:00ሰዓት ላይ ሆኖ የጨረታ ሳጥኑ የሚታሸገው በዛው ቀን 11:00 ሰዓት ላይ ሲሆን ጨረታው የሚከፈተው በሚቀጥለው የሥራ ቀን 25/09/2018.ዓ/ም ከጧቱ 3:00 ሰዓት ላይ ተጫራቾችና ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በማዘጋጃ ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በሚገኝ አዳራሽ ውስጥ ነው፡፡
4. ተጫራቾች የሚያቀርቡት የሊዝ ዋጋ 80% ነጥብ ሲኖረው የቅድሚያ ክፍያ መጠን ደግሞ 12% ነጥብ እና ቀሪ ክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ 8% ይኖረዋል፡፡ የጨረታ አሸናፊ የሚለየው በሶስቱ ነጥቦች ድምር በሚገኝ ውጤት ነው፡፡
5. ተጫራቾች የሚያቀርቡት የቅድሚያ ክፍያ መጠን ከአጠቃላይ የሊዝ ክፍያ ከ20% ማነስ የለበትም
6. የጨረታው አሸናፊ ተለይቶ በማስታወቂያ ሠሌዳ ላይ በግልጽ በይፋ ከተገለፀ በኋላ በጨረታው የተሸነፉ ተጫራቾች ያስያዙት የጨረታ ዋስትና ማስከበሪያ ቦንድ (CPO) ተመላሽ ይደረግለታል፡፡
7. ተጫራቾች ለጨረታው የቀረቡትን ቦታዎች ጨረታው በቦርድ ማስታወቂያና በኤፍ ኤም ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 10/አስር/ በስራ ቀናት ቦታዎቹን ለማሳየት በተመደበው ባለሙያ አማካኝነት ቦታዎቹን በመዘዋወር መመልከት ይቻላል፡፡

ማሳሰቢያ፡-

--ማዘጋጃ ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ በከፊልም ሆነ በሙሉ ጨረታውን የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

--.ማናቸውም ተጨራች ለአንድ ቦታ 3 ተጨራች ቢቀርቡም የዋጋ መቅረቢያ በአግባቡ ካልተሞላ የአቅም ማሳያ እና(cpo)ካለቀረበ ጨረታው ውድቅ ይደረጋል፡፡

--ተጨራቾች የጨረታ ሰነድ ለመግዛት ሲቀርቡ 1 ማንነታቸውን የሚገልፅ መታወቂያ ኮፒ ማቅረብ እንደሚኖርባቸው እንገልፃለን፡፡